# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

## የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት አፈፃፀምና ክትትል

## የብሔራዊ ኮሚቴን ለማቋቋም የወጣ መመሪያ

Record and File
Ministry of Labour and Social Affairs

ግንቦት 2004 ዓ.ም.

አዲስ አበባ።

# የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

# የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት አፈፃፀምና ክትትል

# ብሔራዊ ኮሚቴ ለማቋቋም የወጣ መመሪያ

## አውጭው ባለስልጣን

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 10/5፣እንዲሁም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 30/7 እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 676/2002 ተራ ቁ.3 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት አፈፃፀምና ክትትል ብሔራዊ ኮሚቴ ለማቋቋም የወጣ መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሠጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1. "የአካል ጉዳተኞች መብት ጥበቃ ስምምነት" ማለት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ እ.ኤ.አ ዲሴምበር 13 ቀን 2006 የወጣው ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች መብት ጥበቃ ስምምነት ነው፡፡
2. "ብሔራዊ ኮሚቴ" ማለት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 33/1 ላይ የተጠቀሰውን ተግባራዊ ለማድረግ በመላው ሃገሪቱ የሚቋቋም አስተባባሪ ኮሚቴ ነው፡፡

አብዱልፈታህ አብዱላሂ
ሚኒስትር

3. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

4. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፡፡

5. “የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ” ማለት ጽ/ቤት፣ ኤጀንሲ ወይም በክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ተግባራትን ለማስፈፀም በሕግ የተቋቋመ መንግስታዊ አካል ነው፡፡

6. “መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች” ማለት የውጭ ወይም ሀገር በቀል ሆነው በአካል ጉዳተኞች መብት ዙሪያና ከአካል ጉዳተኝነት ጋር ተያያዥነት ባላቸው ተግባራት ላይ የተሠማሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን ያጠቃልላል፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ለአካል ጉዳተኞች መብት ጥበቃ ስምምነት አፈፃፀምና ክትትል ብሔራዊ ኮሚቴ ለኮሚቴው በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት፣ እንዲሁም ከእዚሁ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለብሔራዊ ኮሚቴ</u>

4. <u>መቋቋም</u>
   1. የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት አፈፃፀምና ክትትል ብሔራዊ ኮሚቴ /ከዚህ በኋላ “ኮሚቴ” እየተባለ የሚጠራ/ በዚህ መመሪያ መሠረት ተቋቁሟል፡፡
   2. ተመሳሳይ ኮሚቴዎች በክልሎች ሊቋቋም ይችላል፡፡

5. <u>የኮሚቴው ኃላፊነትና ተግባር</u>
   1. ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በሚወጡበት ጊዜ የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ጉዳይ ማካተታቸውን ይከታተላል፣ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ሃሣብ ያቀርባል፡፡
   2. የመንግሥት አካላት፣ ሴክተር መሥሪያ ቤቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች



አብዱልፈታህ አብዱላሂ
ሚኒስትር

በእቅዶቻቸውና ፕሮግራሞቻቸው ውስጥ የስምምነቱን ዓላማዎች ማካተታቸውን ያረጋግጣል፤ ያልተካተቱ ከሆነም እንዲካተቱ ጥረት ያደርጋል፡፡

3. ከአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት ድንጋጌዎች ጋር የማይጣጣሙ ሕጎች፣ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲሻሻሉ፣ ልዩ ልዩ የአፈፃፀም ደንቦችና መመሪያዎች እንዲወጡ ለሚመለከታቸው አካላት ሃሳብ ያቀርባል፡፡
4. የአካል ጉዳተኞችን ዕኩል እድል ተጠቃሚነትና ሙሉ ተሳታፊነት ለማረጋገጥ የተቀረፁ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ አፈፃፀማቸውንም ይገመግማል፡፡
5. ለአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነትና ተግባራዊነት የቴክኒክና የማቴሪያል ድጋፍ ስለሚገኝበት መንገድ ሠ.ማ.ጉ.ሚ/ርን ያማክራል፡፡
6. በአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት አፈፃፀም የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት ጥረት ያደርጋል፣ የመፍትሔ እቅጣጫም ይቀይሳል፡፡
7. በአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ስምምነት አተገባበር ላይ መንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ህብረተሰቡ ተባብረውና ተቀናጅተው እንዲሠሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡
8. በአካል ጉዳተኞች መብት ጥበቃ ዙሪያ በዓለም አቀፍ፣ በአህጉርና ሀገር አቀፍ ደረጃ ትብብር፣ የመረጃና የልምድ ልውውጥ ስለሚጠናከርበት ሁኔታ መንገድ ይቀይሳል፡፡
9. በአካል ጉዳተኞች መብት ጥበቃ ስምምነት ዙሪያ የግንዛቤ ማዳበሪያ ፕሮግራሞች የሚጠናከሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡
10. እንደ አስፈላጊነቱ ለስምምነቱ አጋዥ የሆኑ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ያቋቁማል ሥራቸውንም ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
11. ለአካል ጉዳተኞች መብት ጥበቃ ስምምነት አፈፃፀምና ክትትል ዕቅድ ያዘጋጃል፣ የቁጥጥርና ግምገማ ስልት በመንደፍ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ስለሥራ ክንውኑ ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡
12. ለአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ኮንቬንሽን አፈፃፀምና ክትትል የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

ሪከርድና ማህደር
Record and File
Ministry of Labour and Social Affairs

አብዱልፈታህ አብዱላሂ
ሚኒስትር

## 6. የኮሚቴው አባላት

6.1 ከፌደራል የመንግስት መ/ቤቶች፣ ከአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት፣ እንደአግባቡ የፌዴራልና የክልል ባሕሪ ካላቸው መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የተውጣጡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የኮሚቴ አባላት ይኖሩታል፡፡

6.1.1 የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣

6.1.2 የትምህርት ሚኒስቴር፣

6.1.3 የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣

6.1.4 የሴቶች፣የሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፣

6.1.5 የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር፣

6.1.6 የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፣

6.1.7 የኮሚኒኬሽን ጉዳይ ጽ/ቤት፣

6.1.8 የትራንስፖርት ሚኒስቴር፣

6.1.9 ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት፣

6.1.10 የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ክፍል፣

6.1.11 የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት ፌዴሬሽን፣

6.1.12 የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበር፣

6.1.13 የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኛ ሴቶች ብሔራዊ ማህበር፣

6.1.14 የኢትዮጵያ ዓይነ ሥውራን ብሔራዊ ማህበር፣

6.1.15 የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማህበር፣

6.1.16 የኢትዮጵያ ማየትና መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማህበር፣

6.1.17 የኢትዮጵያ ኢንቴሌክቹዋል ዲስቢሊቲ ብሔራዊ ማህበር፣

6.1.18 የኢትዮጵያ ሥጋ ደዌ ተጠቂዎች ብሔራዊ ማህበር፣

6.2 አባልነት ክፍት ሆኖ ይቆያል ሆኖም የምዝገባውን ሁኔታ ኮሚቴው ሊወስን ይችላል፡፡

6.3 የኮሚቴ አባላት በመ/ቤቶቹ /ማህበራቱ የበላይ ኃላፊዎች ይወከላሉ፡፡

6.4 የኮሚቴው ሰብሳቢ በፌዴራል ደረጃ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና በክልል የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ አግባብ ያለው አካል ይሆናል፡፡

6.5 የኮሚቴው ፀሐፊ በየሁለት ዓመቱ በኮሚቴው አባላት ስብሰባ የሚመረጥ ይሆናል፡፡



አብዱልፈታህ አብዱላሂ
ሚኒስትር

7. <u>የኮሚቴው የስብሰባ ጊዜና ምልዓተ ጉባኤ</u>

   1. የኮሚቴው የስብሰባ ጊዜ በስምምነት የሚወሰን ይሆናል፡፡
   2. ከጠቅላላ አባላት ውስጥ 2/3 ኛው ከተገኘ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
   3. በስብሰባ ከተገኙት አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ /50% +.1/ ድምፅ ከተገኘ የኮሚቴው ውሳኔ ይሆናል፡፡ ሆኖም ድምፅ ዕኩል በኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ሁኔታዎች

8. <u>መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ</u>

   ይህ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ ሊሻሻል ይችላል፡፡

9. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

   ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ማንኛውም አካል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

10. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

    ይህ መመሪያ ከግንቦት 14 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት 14 ቀን 2004 ዓ.ም

የፌዴራል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ

ሚኒስቴር ሚኒስትር